# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡
# Ethiopia: The Kingdom of God Services

---

## ለኢትዮጵያ ሰላም፡
## መጸለይ እና መጾም፡ ምን ማለት ነው?

## "ለኢትዮጵያ ሰላም፡ መጸለይ እና መጾም" ማለትማ፡
## "በቅድሚያ፡ ራስን፡ በንስሓ፡
## ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማብቃት!" ማለት ነው፡፡

"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!" "ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!" የሚለውን፡ ሕያው የአምላክ ቃል በመከተል፡ በተለይ፡ ስለኢትዮጵያ ደኅንነትና ሰላም፥ በአጠቃላይም፡ ስለመላው ዓለም፡ በያለንበት፡ የተለየ ጾምና ጸሎት እናደርግ ዘንድ፡ "ሰላም ለኢትዮጵያ" ኀዋ ሰሌዳ (Web Site) ያቀረበውን የተቀደሰ ዓላማ ማሳሰቢያ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፥ የኢትዮጵያ እውነተኞች ወዳጆች የኾኑ ወገኖች ኹሉ ጭምር ተቀብለን፡ በያመቱ ስንፈጽመው መቆየታችን ይታወቃል፡፡

በዚያ ማሳሰቢያ መነሻነት፡ "ሰላም ለኢትዮጵያ"፡ በተለይ፡ ለ፡"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት" ካቀረበው ጥያቄ፡ ባገኘው የተቀባይነት መልስ መሠረት፡ ይኸው ጾምና ጸሎት፡ በያመቱ፡ በዓመቱ እኩሌታ፡ በየካቲት ወር ከሚካኼደው፡ ከሦስት ቀኗ "ጾመ ኢትዮጵያ" ቀጥሎ፡ በዓመቱ የመጨረሻ አጋማሽ ላይ በምትገኘው፡በ፲፫ኛዋ የጳጉሜ ንዑስ ወር ተካኺዶ እንዲፈጸም፡ በስምምነት ተወስኖ፡ ውሳኔው፡ ባለፉት ዓመታት፡ በተግባር ላይ እንዲውል በመደረጉ፡ እነሆ፡ ጣፋጩን ፍሬ፡ ያለማቋረጥ ሲያበረክት ይታያል።

የ"ሰላም ለኢትዮጵያ" ጎዋ ሰሌዳ፡ ይህን ውሳኔ፡ በተግባር ላይ ለማዋል፡ መነሻ ያደረጋቸው መሠረታውያን የኾኑት፡ በቂ ምክንያቶች፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ ባጭር ተገልጸዋል፡፡

፩ኛ. ክህነታዊ ሥልጣንንና ኃላፊነትን የሚጠይቀው፥ በሥርዓትም ሊፈጸም የሚገባው፡ ይኸው አሳብና ውሳኔ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ተጠሪ በኾኑለት፡ በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት" ዋቢነት ተካኺዶ ሊከናወን እንዲችል፡ ፈቃዳቸው በመገኘቱ ነው፤

፪ኛ. በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የዓመቱ፡ "፲፫ኛ (አሥራ ሦስተኛ) እና የመጨረሻዋ ወር" የምትባለው ጳጉሜ፡ ቀድሞም ቢኾን፡ "አዲሱን ዓመት፡ በታደሰ የነፍስ ንቃት፥ የሥጋ ንጽሕናና የመንፈስ ብቅዓት ለመቀበል፡ በሃይማኖታዊ ሥርዓት፡ ቤትንና ቍሳቁሱን ማጥዳት፥ ልብስን ማጠብና ገላን፡ በጠበል ውኃ ማንጻት ብቻ ሳይኾን፡ በኃጢኣት ስሜትና በክፋት ድርጊት ያደፈውን የሰውነትን ውሳጣዊ ኹለንተናም፡ በንስሓ ጭምር ማጥራትና በቅዱስ ቍርባን ማጽደቅ ይገባል!" በሚል እምነት፡ በተለይ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በጾምና በጸሎት የሚያሳልፏት ኾና ስለኖረች ነው፡፡

፫ኛ. በመጀመሪያው ክፍለ ዓመት፡ በየካቲት ወር ለሚካኼደው "ጾመ ኢትዮጵያ" ኹለተኛ ኾኖ፡ በዓመቱ መጨረሻ በጳጉሜ እንዲፈጸም ለተመደበው፡ ለ"ሰላም ለኢትዮጵያ" ጾምና ጸሎት የተወሰነው፡ ይኸው ጊዜ፡ ኢትዮጵያ፡ በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት ኾና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሥ ነገሥትነት፥ በድንግል ማርያም እናት አገርነትና ንግሥትነት፡ በፍጹም ነጻነት የኖረችበትን ፡ የ፯ሺ ፭፻ (የሰባት ሺ አምስት መቶ) ዓመታት ህልውናዋን መታሰቢያ ከምታከብርበት፡ ከታላቁ የ0ውደ ዓመት በዓሏ በኋላ ባለው፡ በ፪ኛው ዓመት ማብቂያና በ፫ኛው ዓመት ዋዜማ ላይ መዋሉ የተለየ አጋጣሚ በመኾኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያ፡ ልጆቿን፡ ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን ይዛ ያሳለፈችው፡ ይህ ያልተቋረጠው የነፃነት ህልውናዋና ብሔራዊ ልዕልናዋ፡ ያለውልውል፡ በበለጠ የሚያረጋግጠው፡ አንድ ጸንቶ የኖረ እውነት አለ፤ ይኸውም፡ ይህች ቅድስት እናት አገር፡ በመለኮታዊው መንግሥት ሥር እየተመራችና እየተዳደረች፥ ልጆቿ ሲያጠፉ፡ በአኹኑ ጊዜ የሚሠቃዩበትን ፈተናና መከራ በመሰለ ፍርድ እየተቀጡ፥ በንስሓ ሲመለሱ ደግሞ፡ አምላካዊ ምሕረትን እያገኙ፡ እርሷ፡ ከነልጆቿ፡ ምንጊዜም፡ በቅዱሱ ኪዳን ተጠብቃ የኖረችና ያለች፥ ወደፊትም የምትኖር መኾኗ ነው፡፡

ከላይ፡ በአርእስቱ እንደተመለከተው፡“ለኢትዮጵያ ሰላም መጸለይ እና መጾም” ማለት "በቅድሚያ፡ ራስን፡ በንስሓ፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማብቃት ማለት ነው!" የተባለው ደግሞ፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል ሊጠቃለል ይቻላል፡- ይህም፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና አምልኮ፡ ታማኝ ኾኖ በመገኘት፥ ምግባሩንና ሥርዓቱንም፡ በትክክል ተከትሎ በመፈጸም፡ ወደፊት ሊመጣ ባለው፡ በዘለዓለማዊው ዓለም ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ፡ እዚሁ፡ <u>አኹን በምንገኝበት፡ በዚህ ዓለም ጭምር፡ ፍጽምትና ሉዓላዊት የኾነችውን መልካሟን ሕይወት፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ መኖር ነው።</u>

ቸሩ ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ ገና ከመጀመሪያው፡ ለአዳምና ሔዋን ሰጥቷቸው፡ እነርሱ ግን ያልፈለጓትንና እንዲያውም፡ በገዛ ምኞታቸውና ፈቃዳቸው፥ ምርጫቸውና ውሳኔያቸው፡ አሽቀንጥረው የጣሏትን፡ ያችን፡ "የእግዚአብሔር ሰላም"፡ ኋላ፡ በመጨረሻው የምሕረት ዘመን፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከአማናዊቷ የሰላም ምንጭ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ ተወልዶ፡ በከፈለው መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ ያችኑ፡ "የእግዚአብሔርን ሰላም" መልሶ፡ ለቅዱሱ ኪዳን እውነተኞችና ታማኞች ኾነው ለተገኙና ለሚገኙ የሰው ልጆች ኹሉ፡ በግል፡ ለእያንዳንዳቸው፥ በጋራም፡ ለኹላቸው፡ "እነሆ፡ በመካከላችሁ ናት!" በማለት ከሰጠ እኮ፡ ዛሬ፡ ኹለት ሺህ ኹለተኛውን ዓመት ጨርሰን፡ እነሆ፡ ኹለት ሺህ ሦስተኛውን ዓመት ልንረከብ ተዘጋጅተናል።

እንግዴህ፡ ያች "ሰላም"፥ አዎን፡ ያች፡ "የእግዚአብሔር ሰላም"፡ በእያንዳንዳችን ሰውነት ውስጥ፥ በመካከላችንም ያለች መኾኗን፥ እንዲሁም፡ ይህን ጾምና ጸሎት እንድናደርግ፡ እጅግ አስፈላጊ የኾነበትን ምክንያት፥ በምን መልክ ልንፈጽመው እንደሚገባም፥ ውጤቱስ ምን ሊኾን እንደቻለና እንደሚችል፡ ሥርዓቱን ጭምር፡ በዝርዝር አብራርተው ያሳውቁን ዘንድ የተዘጋጁት ጽሑፎች፡ ይኸው፡ ከዚህ መልእክት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል። ስለዚህ፡ የተወሰኑትን የጾምና የጸሎት ቀኖች፡ በእውነትና በትክክለኛው አምልኮ ፈጽመናቸው፡ ጣፋጬን ፍሬ ለመሰብሰብ ይቻለን ዘንድ፡ እነዚህን ጽሑፎች፡ ከአኹኗ ዕለት ጀምረን በጥንቃቄና በማስተዋል፥ በጽሙናና በተመስጦ እንመልከታቸው!

መሓሪውና ኃያሉ እግዚአብሔር፡ ኹላችንም፡ ለዚያች፡ ለጳጒሜ የጾምና የጸሎት ቀጠሮአችን የተዘጋጀን ኾነን ለመገኘትና ለመድረስ የበቃን ያድርገን! አሜን።